# “አጽናኑ ሕዝቤን አጽናኑ” (ኢሳይያስ ፵ : ፩)



በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ላለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለማስከበርና በስደትና በመገፋት ውስጥ ያለውን ሕዝበ ክርስቲያን በማጽናናትና በአንድነት በማሰባሰብ ቤተ ክርስቲያንን ሲመራ መቆየቱ ለሁሉም ግልጽ ነው። ቅዱስ ሲኖዶስ በሎስ አንጀለስ ከተማ ባካሄደው አስቸኳይ ልዩ ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ ያጋጠማትን አሳዛኝ ሁኔታ በመገምገም፥ በሐዘን ላይ ያለውን ሕዝባችንን የሚያጽናና ለሥራ የሚያነሳሳ ታላቅ ዓለም አቀፍ የስብከተ ወንጌል ጉባኤ በመላው ዓለም በአስቸኳይ እንዲደረግ በተወሰነው መሠረት ታላቅ መንፈሳዊ የስብከተ ወንጌል ፕሮግራም ተዘጋጅቷል።

## የዚህ ዓለም አቀፋዊ የስብከተ ወንጌል ጉባዔ ዋና ዓላማ

፩. በስደት ላይ ያለው ሕዝበ ክርስቲያን በአንድነት በመጽናትና በመቆም እስከአሁን ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ለማስከበር የከፈለውን መስዋእትነት ዋጋ በመስጠት የበለጠ እንዲበረታ፣ በእምነቱ እንዲጸናና ለእውነት እንዲመሰክር ማድረግ።

፪. ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በተደራጀ ሁኔታ እንዲቀጥል ለማስቻል በአዲስ መንገድ የሚቋቋመውን የመንበረ ፓትርያርክ ሕንጻ ሥራ በገንዘብ፥ በሐሳብና በጉልበት እንዲረዱ ለሕዝበ ክርስቲያን ጥሪ ማድረግ።

፫. ቅዱስ ፓትርያርኩ በግፍ ከመንበረ ፓትርያርካቸው መነሣታቸውን መላው ዓለም እየመሰከረ ባለበት ወቅት በአዲስ አበባ የሚገኙት ጥቂት አባቶች በፖለቲካው ክንድ ተደግፈው የሚነዙትን የሐሰት ምስክርነት ማጋለጥ።

፬. በውጭ ዓለም በስደት የምትገኘውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ሰላም መጠበቅና ማስጠበቅ የሚሉት ተቀዳሚ ይሆናሉ።

ጉባኤው (March 1, 2013)ጀምሮ በዓለም ዙሪያ በህጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥላ ስር ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የሚካሄድ መሆኑን ለመላው ኦርቶዶክሳውያን በአክብሮት እየገለጽን በአካባቢያችሁ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በመከታተል የዚህ ታላቅና ታሪካዊ ጉባኤ በረከት ተሳታፊ እንድትሆኑ ቤተ ክርስቲያን ትጋብዛለች።

# በአሜሪካ ክፍለ ግዛቶችና በዓለም አቀፍ ደረጃ የስብከተ ወንጌል ፕሮግራም

## የሚደረግባቸው ቦታዎችና ጊዜያት



| | | |
|---|---|---|
| 1 | ኒውዮርክ፤ኒውዮርክ | April , 2013 |
| 2 | ባፍሎ፤ኒውዮርክ | March , 2013 |
| 3 | ጀርሲ ሲቲ፤ ኒውጀርሲ | April, 2013 |
| 4 | ዋሽንግተን፤ ዲሲ | March, 2013 |
| 5 | ሻርለት፤ ኖርዝ ካሎሪና | March, 2013 |
| 6 | ኮሎምበስ ፤ኦሃዮ | March, 2013 |
| 7 | አትላንታ ፤ ጆርጅያ | March and April, 2013 |
| 8 | ዴንቨር ፤ ኮለራዶ | March and April, 2013 |
| 9 | ሴንት ፖል፤ ሚኒሶታ | March, 2013 |
| 10 | ጃክሰን ቪል፤ፍሎሪዳ | April, 2013 |
| 11 | ላስቬጋስ፤ ኔቫዳ | March, 2013 |
| 12 | ሳንዲያጎ፤ ካሊፎርንያ | April, 2013 |
| 13 | ሎስ አንጀለስ፤ ካሊፎርንያ | March and April, 2013 |
| 14 | ኦክላንድ፤ ካሊፎርንያ | April, 2013 |
| 15 | ሳክራሜንቶ፤ ካሊፎርንያ | April , 2013 |
| 16 | ሳንሆዜ ፤ ካሊፎርንያ | March, 2013 |
| 17 | ሲያትል፤ ዋሽንግተን | March, 2013 |
| 18 | ሶልት ሌክ ፤ ዩታ | March, 2013 |
| 19 | ሲው ፎልስ፤ ሳውዝ ዳኮታ | March, 2013 |
| 20 | ታምፓ ፤ ፍሎሪዳ | April, 2013 |
| 21 | ባልቲሞር፤ሜሪላንድ | April, 2013 |
| 22 | ሒዩስተን፤ ቴክሳስ | April, 2013 |
| 23 | በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት | March 1, 2013 to May 26, 2013 |
| 24 | በአውሮፓ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት | March 1, 2013 to May 26, 2013 |
| 25 | በአፍሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት | March 1, 2013 to May 26, 2013 |
| 26 | በአውስትራልያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት | Jan. 15, 2013 to May 26, 2013 |
| 27 | በኒውዝላንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት | March 1, 2013 to May 26, 2013 |

“እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፥ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን።”

(፪ኛ ቆሮ. ፩፡፬)